# የግብረገብ ትምህርት

# የመምህር መምሪያ

# ሁለተኛ ክፍል

**ተርጓሚዎች:**

አስመራ ቤጊ

አለሙ አብዲሳ

በርናባስ ደበሎ

ቶለረቢ መኮንን

**አርታዒዎች:**

ትጃኒ ምትኩ

የኔነሽ ሳሙኤል

**የጥራት ገምጋሚ**

ደረጀ መኮንን ዴሬሳ

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቁ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2015/2023

ይህ መጽሐፍ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ2015/2023 ተስማምቶ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው፡፡ የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ በየትኛውም መልኩ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህ መጽሀፍ በትምህርት ሚኒስቴር አመራርና መነሻነት በሀዋሳ ፣ጅማ፣ አዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡ በመቀጠል በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ቅንጅት ተተርጉሞና ተስማምቶ ተዘጋጀ፡፡

ስለዚህ በዚህ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የዩኒቨርስቲ አዘጋጆችና በክልላችን ላሉ የትምህርት ባለሙያ ተርጓሚዎችና አስማሚዎች በሙሉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋና አለው፡፡

## ማውጫ

ምዕራፍ አንድ የራስን ክብርና ደህንነት መጠበቅ ............................ 1

ትምህርት 1. ክብር ............................................................ 2

ትምህርት 3. ክብርን ማሳያና ማሳደግያ መንገዶች ......................... 11

ትምህርት 4. የራስን ደህንነት መጠበቅ ......................................... 15

ትምህርት 5. የህጻናት ደህንነት መጠበቅያ ዜደዎች ........................ 18

ምዕራፍ ሁለት እውነተኛነት እና ታማኝነት .................................... 22

ትምህርት 1. የእውነተኛነት እና ታማኝነት ምንነት ........................ 22

ትምህርት 2. የእውነተኛነት እና ታማኝነት ማሳያዎች .................... 26

ትምህርት 3. ቃልኪዳንን ማክበር .................................................... 30

ትምህርት 4. መስረቅና ማጭበርበርን መጥላት ................................ 33

ምዕራፍ ሶስት ፍትህ ትምህርት 1. የፍትህ ምንነት ........................ 37

ትምህርት 2. ፍትሃዊነት ........................................................ 40

ምዕራፍ አራት መልካም ማህበራዊ ግንኙነት .................................. 43

ትምህርት 1. ጓደኝነት ............................................................ 44

ትምህርት 2. መረዳዳት ........................................................... 48

ትምህርት 3. ጓደኝነትን የሚጎዱ ነገሮች ......................................... 51

ምዕራፍ አምስት ለጋራ ንብረት መጠንቀቅ ...................................... 54

ትምህርት 1. የጋራ ንብረት ....................................................... 54

ትምህርት 2. ውሃ ................................................................. 56

ትምህርት 3. ትምህርት ቤት ..................................................... 58

ትምህርት 4. መንገድ ........................................................ 60

ምዕራፍ ስድስት: ባህላዊ ቅርሶች ........................................................ 62

ትምህርት 1: የባህላዊ ቅርሶች ምንነት ........................................................ 62

ትምህርት 2: የባህላዊ ቅርሶች ዓይነቶች ........................................................ 66

ትምህርት 3: የባህላዊ ቅርሶች ጥቅም ........................................................ 69

ትምህርት 4: ባህላዊ ቅርሶችን መንከባከብ ........................................................ 71

የግብረገብ ትምህርት መርሃትምህርት ሁለተኛ ክፍል ........................ 74

# ምዕራፍ አንድ

## የራስን ክብርና ደህንነት መጠበቅ

(ክፍለጊዜ 18)

### መግቢያ

ይህ ምዕራፍ አምስት ዋና ዋና ርዕሶች አሉት፡፡ እነሱም፡- አክብሮት፣ የአክብሮት አስፈላጊነት፣አክብሮትን ማሳያና ማሳደጊያ መንገዶች፣የራስን ደህንነት መጠበቅና የህጻናት ደህንነት መጠበቅያ ዜደዎች ናቸው፡፡ ለሁሉም ትምህርቶች አጫጭር ማብራሪያ በተማሪው መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ ጠቃሚ ማስታወሻዎችም በመምህራን መምሪያ መጽሃፍ ውስጥም ተካቷል፡፡

### የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- የክብርን ምንነት ያብራራሉ ፤
- የክብርን አስፈላጊነት ይናገራሉ፤
- የራስን ደህንነት ማስጠበቂያ ዜዴዎች ይዘረዝራሉ፤
- ክብር እንዴት እንደሚገለጽ ይለያሉ፤
- ጉዳት ከሚያደርሱ ነገሮች ራሳቸውን ይጠብቃሉ፡፡

## ትምህርት 1. ክብር

**ተማሪዎች ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት**

- የክብርን ምንነት ይገልጻሉ፡፡

መምህር/ት፣ የተማሪዎቹን የቀደመ እውቀት የሚያነቃቃ የግንዛቤ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ ጥያቄውን በማቅረብ ተማሪዎች በጥያቄው ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም የተማሪዎችን መልስ ይቀበሏቸው፡፡ በተማሪዎቹ ምላሽ ላይ በቂ ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም ከተማሪ መማሪያ መጽሀፍ ላይ ማስታወሻውን አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው፤ ተማሪዎቹም እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

**ማስታወሻ**

ክብር በብዙ መንገዶች ሊገለጽ እንደሚችል ይንገሯቸው፡፡ ለምሳሌ፡

- ታላላቆችን ማክበር
- ለታላላቆች መታዘዝ
- ሰውን አለመሳደብ
- ለአቅመደካሞችና ለአካል ጉዳተኘ ቅድሚያ መስጠት ወዘተ

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የግንዛቤ ጥያቄ ለመግቢያ ያህል ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠልም ክብርን መሰረት ያደረገ ማስታወሻ ከመስጠትዎ በፊት ስለክብር ለግንዛቤ እንዲረዳቸው ገለጻ ያድርጉላቸው፡፡ ከዚያም በራስ መደሰትን የሚያመለክት በቀረበው ምስል ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎቹ ከምስሉ የተገነዘቡትን እንዲያስቡ በማስታወስ የቀረበላቸውን የተግባር ጥያቄ ጥንድ ጥንድ ሆነው ለመወያየት እንዲዘጋጁ በማድረግ በጥያቄው ላይ ያወያዩዋቸው፡፡

በመርጃ መሳሪያነት ተንቀሳቃሽ ሞባይል ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን ፣የተለያዩ ምስሎችን በመጠቀም እስፖርተኞች በተሰማሩበት መስክ አሸንፈው በራሳቸው ሲኮሩ የሚያመለክት ለተማሪዎች በማሳየት ትምህርቱን ተጨባጭ ማድረግ ይቻላል፡፡

**ተግባር 1.**

ተማሪዎች የቀረበው ምስል ምን እንደሚያመለክት ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ከጥንዶቹ አንድ ተማሪ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍል እንዲያቀርብ ያበረታቱ፡፡ በቀረበው ሀሳብ ላይ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ተግባር 2.**

1. "ቤተሰብና ጎረቤታችንን ማገዝ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ማስታወሻና ምስሎች በመመልከት በቀረቡት መወያያ ሀሳቦች ላይ በቡድን በመወያየት ሀሳባቸውን ለእርስዎ እንዲናገሩ ይዘዟቸው፡፡ ከተማሪዎቹ መልስ በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡
2. ይህንን ጥያቄ በሚከተለው መልኩ እንዲመልሱ ይጠበቃል፡፡ ልጆች ጎረቤቶቻቸውን ውሃ በመቅዳት፣ ቡና በማፍላት፣ ጭቃ በማቡካት፣ እንጨት በመልቀምና ለሎችንም ሥራዎች በመሥራት በስራ ማገዝ እንደሚችሉ ያስገንዝበቧቸው፡፡ ተማሪዎችም ቤተሰብን እና ጎረቤትን መርዳት ጨዋነት መሆኑን መገንዘብ እንዳለባቸው ይግለጹላቸው፡፡ በውይይታቸውም መጨረሻ ገንቢ የሆነ አስተያየት ይስጧቸው፡፡

በተራ ቁጥር 3 እና 4 ለቀረቡት ጥያቄዎች እውነት ወይም ውሸት በማለት እንዲመልሱ በማድረግ እውነት ወይም ውሸት

ያሉበትን ምክንያት እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። ይህም ተማሪዎቹ ለሰጡት መልስ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ለመረዳት ያግዛል። ከተማሪዎቹም የሚከተሉት መልሶች ይጠበቃሉ።

3. ውሸት

4. እውነት

**ተግባር 3.**

“የግለሰቦችን ልዩነት ማድነቅና ማክበር” በሚል የሉባባ እና የዱሬሳ ጭውውት ቀርቧል። ጭውውቱን እንዲያነቡ በማድረግ በተግባር 3. ላይ የቀረበውን የመወያያ ጥያቄ ያሰሯቸው።

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያለው ተግባር 3. “የግለሰቦችን ልዩነት ማድነቅና ማክበር” ከሚል ርዕስ ስር የቀረበው ጭውውት ላይ የተመሰረተ ነው። ንግግሩም ሉባባ እና ዱሬሳ የከሚሴ የኦሮሞ ብሄረሰብ እና የሲዳማ የባህል ልብስ ለብሰው ሲያደንቁ ያሳያል። ተማሪዎች በመጽሃፋቸው ላይ ባለው ሥዕል ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ። ከዚያም የተረዱትን በክፍል ውስጥ ማብራሪያ እንዲሰጡ ያበረታቱ።

1. ሉባባና ዱሬሳ የባህል ልብሳቸውን ቀለም እና የስማቸውን ትርጉም ያደንቁ ነበር። ይህ ደግሞ መልካም አስተያየት፣ ፍቅርን እና እርስ በርስ መከባበርን ያመለክታል። ተማሪዎችም የግለሰብ ልዩነቶችን በማድነቅ እና በማክበር

እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በውይይታቸው መጨረሻ የግል ልዩነቶችን ማክበር አስፈላጊ እንደሆነ በመግለጽ ለተማሪዎች ገንቢ አስተያየት ይስጧቸው፡፡

2. በሁለተኛው ትዕዛዝ ስር ከላይ በቀረበላቸው ጭውውት ላይ መሰረት በማድረግ ለቀረበው ጥያቄ ሀሳቡን በማንበብ እውነት/ውሸት በማለት እንዲመልሱ ያበረታቷቸው፡፡ ለመልሳቸውም ምክንያታዊ እንዲሆኑ ለምን እውነት/ውሸት እንዳሉ ይጠይቋቸው፡፡ ተማሪዎቹ የሚሰጡት መልስ ***"ውሸት"*** የሚል እንዲሆን ይጠበቃል፡፡

ምዘና

**በዚህ ትምህርት ስር የሚከተሉትን የምዘና ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡**

- የቅድመ ትምህርት ግንዛቤ ጥያቄዎች
- የመወያያ ጥያቄዎች
- እውነት/ውሸት ጥያቄዎች
- ምልከታ ወዘተ
- ተከታታይ ምዘናዎችን፣ የቃል ጥያቄዎችን እና ምልከታን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡
- ተማሪዎች የቀረበላቸውን ጥያቄ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ለውጥ ይመዝግቡ፡፡

- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው።
- በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት በጣም ጥሩ ነው! በማለት ያበረታቱ።

## ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

- ክብር ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፣

የክብር አስፈላጊነት በሚል የቀረበውን ርዕስ ማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ርዕሱን በማስተዋወቅ ለቅድመ ግንዛቤ የቀረበውን ጥያቄ በማቅረብ ያወያዩዋቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል በተማሪዎች መማሪያ መጽሃፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ ተማሪዎችም ደጋግመው እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የግንዛቤ ጥያቄዎች ለመግቢያ ያህል ይጠይቋቸው፡፡ በመቀጠልም በተማሪ መጽሐፉ ላይ ያለውን ሥዕል በተመለከተ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች ከሥዕሉ የተረዱትን ለክፍሉ እንዲያካፍሉ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል በመልሶቻቸው ላይ አስተያየት ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም ለተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ አጭር ማስታወሻ ይስጡ፡፡

በተጨማሪም፣ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ተግባር ለተማሪዎች ያንብቡና ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡ በመጨረሻም፣ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በዚህ ትምህርት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

በመርጃ መሳሪያነት ሰዎች ሲከባበሩ የሚያመለክቱ ምስሎችን፣ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠቀም ሰዎች ሲከባበሩ የሚያመለክቱ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በመጠቀም ትምህርቱን ተጨባጭ ያድርጉ፡፡

**ምዘና**

ለምዘና የሚከተሉትን መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ምልከታ
- የቃል ጥያቄ
- የተግባር ጥያቄዎች

ተከታታይ ምዘናዎችን፣ የቃል ጥያቄዎችንና ምልከታን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታቸው ይመዝግቡ፡፡
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ራዎችን ይስጧቸው፡፡
- በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ፡፡ ለምሳሌ: ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት “በጣም ጥሩ ነው” በማለት ያበረታቱ፡፡

**ተግባር 4.**

1. ተማሪዎች ስለ ክብር አስፈላጊነት በተዘጋጀው ጥያቄ ቁጥር 1ና2 ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ሰውን ማክበር

ራስንም ማክበር እንደሆነ፣ ለሌሎች የሚገባቸውን ክብር መስጠት ለጠንካራ በራስ የመተማመን እና የራሳችን ውሳኔ እንዲኖረን አስፈላጊ መሆኑን፣

2. ሌሎች ሰዎች እንዲያከብሯቸው እነሱ ሰውን ማክበር እንዳለባቸው ይንገሯቸው፡፡

   ተማሪዎች መዋደድ ክብር እንደሚያሳይ ማወቅ አለባቸው፡፡ ለራሳቸውና ለሌሎች ሰዎች ክብር መስጠታቸው ትልቅ ፋይዳ እንዳለው በምሳሌ በማስደገፍ ይግለጹላቸው፡፡

3. መከባበር ጓደኝነትን እንደሚያጠናክር ያላቸውን ሀሳብ ከተሰጡት አማራጮች እንዲመርጡ በማድረግ ሀሳባቸውን ያጠናክሩ፡፡

## ትምህርት 3. ክብርን ማሳያና ማሳደግያ መንገዶች

ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገቧቸው የመማር ብቃቶች፣

- ክብርን እንዴት ማሳየት እንደሚቻል ይናገራሉ፤
- የክብር አሰጣጥ ማጎልክበቻ መንገዶችን ይለያሉ።

የትምህርት ይዘቱን ከማቅረብዎ በፊት ለቅድመ ግንዛቤ የቀረበውን ጥያቄ በማቅረብ ያወያዩዋቸው። በመቀጠል ማስታወሻውን አንድ ጊዜ ለተማሪዎች በማንበብ ተማሪዎቹም ደጋግመው እንዲያነቡ ይዘዟቸው። ማስታወሻውንም በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው።

### ማስታወሻ

አክብሮት በብዙ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። ለምሳሌ፣

- በትምህርት ቤት ውስጥ የደንብ ልብስ በመልበስ፣
- መምህሩ ጥያቄ ሲጠይቅ እጅን በማንሳት ምላሽ መስጠት፣
- መምህራን ወደ ክፍል ሲገቡ ተነስቶ መቀበል፤
- መምህሩ በሚያስተምርበት ጊዜ በደንብ መከታተል፣
- ታላላቆችን ማክበር፤
- እናት እና አባትን ማክበር፤
- እርስ በርሳችሁ መከባበር፤
- ማጭበርበርና መስረቅን መተው፤
- ጥያቄዎችን እጅ በማውጣት መጠየቅ እና መመለስ ናቸው።

ክብርን ከሚያጎለብቱበት መንገዶች መካከል ከታላላቆቻቸው ምክር በመስማት፣ የመምህራኖቻቸውን ምክር በመስማት የክብርን አሰጣጥ እንደሚያጎለብቱ ይንገሯቸው፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

መምህር/ት፣ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረውን የግንዛቤ ጥያቄ ለመግቢያ ያህል ይጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፣ "ለቤተሰባችሁና ለአዛውንቶች ያላችሁን አክብሮት እንዴት ታሳያላችሁ?" ብሎ የቀረበውን ጥያቄ መጠየቅ፡፡ ሥዕሎቹም አስተማሪ ክፍል ሲገባ ተነስተው መቀበል፣ እጅ በማውጣት ጥያቄ መጠየቅና መልስ መስጠት እንዲሁም የአከባቢያችን ቆሻሻ ሰብስበን ወደ ጉድጓድ መጣል፣ ችግኝ መትከልና ውሃ ማጠጣትን ያሳያሉ፡፡ በመቀጠል በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያለው ሥዕል ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ሐሳባቸውን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያድርጉና በመልሶቻቸው ላይ አስተያየት ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም ለተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ አጭር ማስታወሻ ይስጡ፡፡

በአጠቃላይ፣ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ተግባር ለተማሪዎች ያንብቡና ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡ መረዳታቸውንም ለማረጋገጥ በዚህ ትምህርት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

በመርጃ መሳሪያነት ተማሪዎች ክብርን የሚያዳብሩበት ዘዴ የሚያመለክቱ ምስሎችን፣ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ

መሳሪያዎችን በመጠቀም ልጆች የተለያዩ ሰዎችንና ድርጊቶችን በክብር ሲተገብሩ የሚያመለክቱ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በመጠቀም ትምህርቱን ተጨባጭ ያድርጉ፡፡

**ምዘና**

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ፡፡
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው፡፡

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ፡፡ ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት “በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው” በማለት ያበረታቷቸው፡፡

**ተግባር 5.**

በዚህ ስር ለቀረቡት ጥያቄዎች የሚከተሉት መልሶች ከተማሪዎች ይጠበቃሉ፡፡ መልሶቹን በትኩረት በመከታተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ ለመምህራን ያለንን ክብር ከምንገልጽባቸው መንገዶች መምህራን ክፍል ሲገቡ ተነስቶ መቀበል፣ እጅ አውጥቶ ጥያቄ መጠየቅና መመለስ ሊጠቀሱ

ይችላሉ፡፡

ክብርን ለማግኘት ታላላቆችን ማክበር፣ እናትና አባትን ማክበር ፣ ታላቅና ታናሽ መከባበር ፣ ከሌብነትና ማታለል መራቅ፣ መንገድ ላይ አለመሸናት ይጠቀሳሉ፡፡

## ትምህርት 4. የራስን ደህንነት መጠበቅ

**ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች፣**

- ደህንነታችን ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን ይዘረዝራሉ፤
- ደህንነታችንን የምንጠብቅባቸው ዜደዎች ይናገራሉ፡፡

የትምህርት ይዘቱን ከማቅረብዎ በፊት ለቅድመ ግንዛቤ የቀረበውን ጥያቄ በማቅረብ ያወያዩዋቸው፡፡ በመቀጠል ማስታወሻውን አንድ ጊዜ ለተማሪዎች በማንበብ ተማሪዎቹም ደጋግመው እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡ ማስታወሻውንም በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

**ማስታወሻ**

እራስን መጠበቅ ማለት አደገኛ እና ጎጂ ከሆኑ ነገሮች እራስን መከላከል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጎጂ ከሆኑ ነገሮች ሁሉ መራቅ አለብን፡፡ ልጆች ጥንቃቄ ካላደረጉ ለብዙ ጉዳቶች ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

ስለዚህ፣ ደህንነታቸውን ለመጠበቅ፡-

- በስለታማ ነገሮች መጫወትን ማስወገድ፣
- መንገድ ሲያቋርጡ ግራ እና ቀኝ መመልከት፣
- መንገድ ሲያቋርጡ የዜብራ (በአስፓልት ላይ ለእግረኛ ማቋረጫ የተሰመረውን መስመር በመያዝ) ምልክቶችን በማየት ማቋረጥ፣
- የግል እና የአካባቢ ንፅህናን መጠበቅ፣

- ጎጂ ከሆኑ ነገሮች መራቅ::

ለምሳሌ፡- በእሳት ከመጫወት፣ የቤትና የዱር እንስሳት፣ እንደ ድመት፣ ቀበሮ፣ ከብቶች እና ሌሎች እንስሳትን ሳያውቁ አለመንካት::

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር/ት፣ በመጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ ለግንዛቤ ማዳበሪያ የቀረበውን “ደህንነታችንን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?” በሚል በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ጥያቄ ለመግቢያ ያህል ይጠይቋቸው:: በመቀጠል በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያለውን እያንዳንዱ ሥዕል ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ:: ከዚያም ተማሪዎች ከሥዕሉ የተረዱትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያድርጉ:: በመልሶቻቸውም ላይ አስተያየት ይስጧቸው:: በመቀጠል ለተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ አጭር ማስታወሻ ይስጡ::

በተጨማሪም፣ በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ተግባር ለተማሪዎች____በማቅረብ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው:: በመጨረሻም፣ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በዚህ ትምህርት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው::

በመርጃ መሳሪያነት የራስን ደህንነት ሊጎዱ የሚችሉ ስለት ያላቸውን መሳሪያዎች፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ወይም ምስሎችን

በመጠቀም የትራፊክ መንገድ አጠቃቀምን በማመልከት ትመምህርቱን ተጨባጭ ያድርጉ፡፡

**ምዘና**

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ፡፡
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው፡፡

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ፡፡ ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት "በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው" በማለት ያበረታቷቸው፡፡

**ተግባር 6.**

ተማሪዎች በተራ ቁጥር 1-4 ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በሚከተለው መልኩ ለመመለስ ይችላሉ፡፡ ይህንንም በመከታተል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

1. ደህንነታችን ለመጠበቅ ብዙ ነገሮች ማድረግ እንችላለን፣ ለምሳሌ:
    - ስለታማ በሆኑ ነገሮች ከመጫወት መቆጠብ/መራቅ
    - መንገድ ስናቋርጥ ግራ እና ቀኝ መመልከት

- የዜብራ ምልክትን እያየን መሻገር
- የግል እና የአካባቢ ንፅሕናን መጠበቅ

2. እውነት

3. መ

4. በመኖሪያ አከባቢ ደህንነትህን ለመጠበቅ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ታደርጋለህ ለሚለው ብዙ ነገሮችን መጥቀስ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ
    - እጃችን እና ፊታችንን መታጠብ፣
    - ከምግብ በፊት እና በኋላ እጅን መታጠብ፣
    - ልብሳችን ማጠብ፣
    - በሹል ነገሮች ከመጫወት መቆጠብ፣
    - የመኪና መንገድ ብቻችን አለመሻገር፣
    - አደገኛ እና ጎጂ ከሆኑ ነገሮች መራቅ፣

## ትምህርት 5. የህጻናት ደህንነት መጠበቂያ ዜደዎች

ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት፣

- ሕፃናት ደህንነታቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ ይዘረዝራሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን “ከቤት ወደ ትምህርት ቤት ስትሄዱ ደህንነትህን/ሽን እንዴት ትጠብቃለህ/ቂያለሽ?” የሚለው በተማሪ መጽሐፍ የቀረበውን

ጥያቄ ለመግቢያ ያህል ይጠይቋቸው:: በመቀጠልም በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያለውን እያንዳንዱ ሥዕል ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ:: ከዚያም ተማሪዎች ከሥዕሉ የተረዱትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያካፍሉ ያድርጉ:: በመልሶቻቸውም ላይ አስተያየት ይስጧቸው:: በመቀጠል በተማሪዎች መጽሃፍ ላይ ያለውን ማስታወሻ ለተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉላቸው:: በተጨማሪም፣ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ተግባር 7. ለተማሪዎች በማንበብ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው:: በመጨረሻም፣ ተማሪቹ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ '√' ምልክት በማድረግ ያረጋግጡ::

**ምዘና**

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል:: እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ::

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ::
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ::
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው::

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ:: ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት "በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው" በማለት ያበረታቷቸው::

**ተግባር 7. የተሰጠው ድርጊት የሕፃናትን ደህንነት የሚያስጠብቅ እና የማያስጠብቅ መሆኑን { √} ምልክት በማመልከት ያረጋግጡ፡፡**

| ቁ. | ድርግቶች | የማያስጠብቅ | የሚያስጠብቅ |
|---|---|---|---|
| 1 | ብታቸውን ውሃ መዋኘት | { √} | |
| 2 | ከምግብ በፍትና በኂላ እጅ መታጠብ | | { √} |
| 3 | ስለት ባላቸው መሣሪያዎች መጫወት | { √} | |
| 4 | የቤተሰብን ምክር መስማት | | { √} |
| 5 | እንስሳትንማባረርና በእጅ ለመያዝ መሞከር | { √} | |
| 6 | ግራና ቀኝ በመመልከት መንገድ መሻገር | | { √} |
| 7 | ከአቅማችን በላይ የሆነ ሥራ መሥራት | { √} | |
| 8 | የቤቴሰባችንን ስልክ ቁጥር ማወቅ | | { √} |
| 9 | የአከባቢያችንን ንፅሕና መጠበቅ | | { √} |
| 10 | ሰውን መሳደብ | { √} | |

## የክለሳ ጥያቄ መልሶች

| I. እውነት/ሐሰት | | II. ምርጫ |
|---|---|---|
| 1. | ውሸት | 1. ለ |
| 2. | እውነት | 2. መ |
| 3. | እውነት | 3. ሐ |
| 4. | እውነት | 4. መ |
| 5. | እውነት | 5. ሐ |

# ምዕራፍ ሁለት
# እውነተኛነት እና ታማኝነት

(ክፍለጊዜ 20)

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ አራት የትምህርት ይዘቶች አሉት፡፡ እነዚህም፡- የእውነተኛነትና እና የታማኝነት ምንነት፣ የእውነተኛነት እና የታማኝነት ማሳያዎች፣ቃልኪዳንን ማክበርና የመስረቅ እና ማጭበርበርን መጥላት ናቸው፡፡ ለሁሉም ትምህርቶች አጭር ማብራሪያዎች በተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ እንዲሁም ተጨማሪ ማስታወሻዎች በዚህ በመምህሩ መምርያ ውስጥ ተካተዋል፡፡

## የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

- የእውነተኛነት እና ታማኝነት ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የእውነተኛነት እና የታማማኝነት አመልካቾችን ይናገራሉ፡፡

## ትምህርት 1. የእውነተኛነት እና ታማኝነት ምንነት

### ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት

- የእውተኛነትን እና የታማኝነትን ምንነት ይገልጻሉ፡፡

መምህር/ት በዚህ የትምህርት ርዕስ ስር ለግንዛቤ የቀረበውን ጥያቄ “እውነት መናገር ምን ፋይዳ አለው?” በማሰራት የቀደመ እውቀታቸውን ያነቃቁ፡፡ ከተማሪዎቹ የቀረቡትን ምላሾች መሰረት በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል ስለእውነተኛነትና ታማኝነት አጭር ማስታወሻ ቀርቧል፡፡ ማስታወሻውን መሰረት በማድረግ ተማሪዎችዎ በግብረገብ የታነጹ እንዲሆኑ ከአከባቢዎ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማቀናጀትና የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ትምህርቱን ያቅርቡ፡፡ የቀረቡትንም ተግባራት ያሰሯቸው፡፡

**ማስታወሻ**

ልጆች እውነት ተናጋሪ እንጂ ውሸታም መሆን የለባቸውም፡፡ እውነትን የሚናገር ሰው ታማኝ ስለሆነ በሁሉም ሰው ዘንድ ይወደዳል፡፡ ታማኝ መሆን ከውሸት እና ከማጭበርበር መራቅ ነው፡፡

እውነተኛነትና ታማኝነት ከሚጠናከርባቸው መንገዶች ጥቂቶቹ ፡-

- ለእውነት እና ለታማኝነት ቦታ መስጠት
- እውነት መናገር
- ለእውነት ምሳሌ መሆን
- ለተማሪዎች ትክክለኛውን መንገድ ማሳየት፡፡
- ለድርጊታቸው አስተያየት መስጠትና ማበረታታት
- ስህተቶች ማረም
- ቃላቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው መንገር

- ለሰዎች ንብረት ጥንቃቄ ማድረግና የመሳሰሉት

## የመማር እና የማስተማር ዘዴዎች

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የእውተኛነትን እና የታማኝነትን ምንነት ትገልጻለህ/ሽ" በሚል በተማሪ መጽሐፍ የቀረበውን ጥያቄ ለመግቢያ ያህል ይጠይቋቸው። ከዚያም በኂላ ሐሳባቸውን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያድርጉና በመልሶቻቸው ላይ አስተያየት ይስጧቸው። በመቀጠል ለተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ አጭር ማስታወሻ ይስጡ።

በተጨማሪም፣ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ተግባር ለተማሪዎች በማቅረብ ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ ያበረታቱ። በመጨረሻም፣ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

በመርጃ መሳሪያነት የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠቀም መተማመንን የሚያመለክቱ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን፣ ፎቶግራፎችን፣ የዝንጀሮና የአይጥ ምስሎችን በመጠቀም የሚተላለፈውን የዝንጀሮና የአይጥ ታሪክ ተጨባጭ ያድርጉ።

## ምዘና

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል። እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ።

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ።
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ።
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው።

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት “በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው” በማለት ያበረታቷቸው።

**ተግባር 1.**

ይሄን ጥያቄ ለመመለስ ተማሪዎች በብዙ መንገድ ሊሞክሩ ይችላሉ። ይህ ተግባር ተማሪዎች እውነት እንዲናገሩ እና እንዲተገብሩ ያደሪጋል። ተማሪዎች በሁሉም ቦታ እውነት መናገር እንዳለባቸው መምከር አስፈላጊ ነው። ለእውነት ሀሰት ጥያቄዎችም ከተማሪዎች የሚከተለው መልስ ይጠበቃል።

1. እውነት
2. እውነት

## ትምህርት 2. የእውነተኛነት እና ታማኝነት ማሳያዎች

**ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች**

- የእውነተኛነት እና የታማኝነት ማሳያዎችን ይዘረዝራሉ፤
- እውነት መናገር ያለውን ፋይዳ ይናገራሉ፡፡

መምህር/ት በዚህ የትምህርት ርዕስ ስር ለግንዛቤ የቀረበውን ጥያቄ "እውነተኛነት እና ታማኝነት በምን በምን ተግባራት ሊገለጹ ይችላሉ?" በማሰራት የቀደመ እውቀታቸውን ያነቃቁ፡፡ ከተማሪዎቹ የቀረቡትን ምላሾች መሰረት በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል ስለእውነተኛነትና ታማኝነት ማሳያዎች አጭር ማስታወሻ ቀርቧል፡፡ ማስታወሻውን መሰረት በማድረግ ተማሪዎችዎ እውነተኛነትና ታማኝነት በምን እንደሚገለጹ ከአከባቢዎ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማቀናጀትና የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ትምህርቱን ያቅርቡ፡፡ የቀረቡትንም ተግባራት ያሰሯቸው፡፡

**ማስታወሻ**

እውነተኝነትንና ታማኝነትን በብዙ መንገዶች ማሳየት እንችላለን፡፡ እነዚህም፡- እውነትን መናገር፣ ቃል ኪዳንን መጠበቅ፣ ሌብነትን እና ማታለልን መጥላትና ወዘተ ናቸው፡፡ ልጆች እውነትን መናገር እንጂ ውሸትን መናገር የለባቸውም፡፡ እውነተኛ ሰው በእናት እና በአባት ይወደዳል፡፡ እንዲሁም በጓደኞች፣ በአስተማሪዎች እና በጎረቤቶች ይወደዳሉ፡፡ እውነትን መናገር

በጎነት ነው፡፡ በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ “እውነት የፈጣሪ ልጅ ነው፡፡” ይባላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የኦሮሞ ማህበረሰብ “ያለ እውነት አያሸንፉም፣ ቢያሸንፉም አያዛልቅም” ይላል፡፡ የእውነትን እና የታማኝነትን ሀሳብ በበለጠ ለማሳየት የዝንጀሮ እና የአይጥ ታሪክ እንደማሳያ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህንንም ታሪክ ከተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ያንብቡላቸው፡፡

**የመማር እና የማስተማር ዘዴዎች**

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን “እውነተኛነት እና ታማኝነት በምን በምን ተግባራት ሊገለጹ ይችላሉ?” በሚል በተማሪ መጽሐፍ የቀረበውን ጥያቄ ለመግቢያ ያህል ይጠይቋቸው፡፡ እውነተኛነት እና ታማኝነት በብዙ ሁኔታዎች ሊገለጹ እንደሚችሉ ምሳሌ በመጥቀስ ያስገንዝቧቸው፡፡ በመቀጠልም በተማሪ መጽሐፉ ላይ ያለውን ሥዕል ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከዚያም ተማሪዎች ከሥዕሉ የተረዱትን ለክፍሉ እንዲያካፍሉ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ለተማሪዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ አጭር ማስታወሻ ይስጡ፡፡

በተጨማሪም፣ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ተግባር ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ምን እንደተረዱ

ይጠይቋቸው። በመጨረሻም፣ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

**ምዘና**

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል። እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ።

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ።
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ።
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው።

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት "በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው" በማለት ያበረታቷቸው።

**ተግባር 2.**

ከተራ ቁጥር 1-3 ያሉት ጥያቄዎች ቀርበዋል። በስራቸውም አራት አራት አማራጭ መልሶች ቀርበዋል። ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛውን መልስ እንዲመርጡ ያበረታቷቸው። ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው።

1. መ  2. ሐ  3. መ

**ተግባር 2.** ጥያቄ 3 የሚያተኩረው የእውነት ተናገሪ ባህሪያት ላይ ነው፡፡ እውነት መናገርን የሚያሳዩ ብዙ አባባሎች አሉ፡፡ ሰዎች አክብሮትን፣ ወጎችን ለመግለጽ በተለያየ መንገድ ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ “እውነት ትቀጥናለች እንጂ አትቆረጥም፡፡” ይህ ማለት የቱንም ያህል ውሸት ቢበዛ እውነትን ሊያጠፋ አይችልም ማለት ነው፡፡ “እውነትን ተናግሮ በመሸበት ማደር፡፡” ይህ ምሳሌ የሚያሳየን ሰዎች እውነት በመናገራችን ቢጠሉንም ለእውነት መጠላታችን መልካም ነው፡፡

**ተግባር 3.**

በዚህ ስር ከተራ ቁጥር 1-4 ለቀረቡት የተግባር ጥያቄዎች ከተማሪዎች የሚከተሉት መልሶች ይጠበቃሉ፡፡ እርስዎም ይህንኑ በመከታተል ተገበውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

1. ውሸት
2. እውነት
3. እውነት
4. በዚህ ታሪክ ውስጥ እውነት የነበረው ዝንጀሮ መሆኑን ይንገሯቸው፡፡ አይጧ የሞተችው ውሸት በመናገሯ እንደሆነ ከታሪኩ መረዳት እንደሚቻል፣ እውነትን መናገር ከተለያዩ ችግሮች ማዳን እንደሚችል ያስገንዝቧቸው፡፡ ስለዚህ ዝንጀሮ እውነት በመናገሩ ከሞት እንዴት እደተረፈ ተማሪዎቹ በቡድን እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡

## ትምህርት 3. ቃልኪዳንን ማክበር

### ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት

- ቃልኪዳን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይለያሉ፡፡
- ቃልኪዳንን ማክበር ያለው ፋይዳ ይገልጻሉ፡፡

መምህር/ት በዚህ የትምህርት ይዘት ስር "አንድን ነገር እሰራለሁ ብለህ/ሽ ለወላጆችህ/ሽ ቃል ገብተህ/ሽ ታውቃለህ/ሽ?" በሚል የቀረበውን የግንዛቤ ጥያቄ በማቅረብ የቀደመ እውቀታቸውን ያነቃቁ፡፡ በመቀጠል ሰዎች በምን በምን ሁኔታ ውስጥ ቃልኪዳን እንደሚገቡ (ለምሳሌ፡ በጋብቻ ጊዜ፣ልጅ በጉዲፈቻ ሲወስዱ፣በሰለጠኑበት የትምህርት መስክ ሲመረቁ...) ከተማሪዎች አከባቢ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማቀናጀት ለተማሪዎች ትምህርቱን ያቅርቡ፡፡

### ማስታወሻ

ቃል መግባት ማለት የተስማሙበትን ነገር ፈጽመው መገኘት ነው፡፡ ቃል ኪዳን ማለት መሀላ ነው፡፡ አልዋሽም ወይም አልከዳም ብሎ ቃል መግባት ነው፡፡ ቃልኪዳንን ማፍረስ ነውር ነው፣ ቃልኪዳንን ማፍረስ ውርደትን ያስከትላል፡፡ በኦሮሞ ባህል ልጆች አዋቂዎችን አይዋሹም፡፡ በሐሰት አይመሰክሩም፡፡ ውሸታም ካዩ ይመክሩታል፤ሁለተኛ እንዳይዋሽ ያስጠነቅቁታል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን "አንድነገር እሠራለሁ ብለህ/ሽ ለቤቴሰቦችህ/ሽ ቃል ገብተህ/ሽ ታውቃለህ?" የሚለውን የግንዛቤ ጥያቄ ይጠይቁ፡፡ በመቀጠል በተማሪ መጽሐፍ ላይ ያለውን የፍየልና የቀበሮ ታሪክ ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ የቀረበውን ተግባር በማንበብ ያሰሯቸው፡፡ በመጨረሻም፣ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በዚህ ትምህርት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

በመርጃ መሳሪያነት የቀበሮና የፍየል ምስል በተለያዩ አማራጮች ማለትም በተንቀሳቃሽ ምስል ሊሆን ይችላል መማሪያ ክፍል በማቅረብ የቀበሮንና የፍየልን ታሪክ ተጨባጭ በማድረግ ያቅርቡ፡፡

### ምዘና

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ፡፡
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው፡፡

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት “በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው” በማለት ያበረታቷቸው።

**ተግባር 4.**

በዚህ ተግባር ስር የምርጫና የእውነት/ውሸት ጥያቄዎች ቀርበዋል። እነዚህን ጥያቄዎች በማቅረብ ተማሪዎች እንዲሰሩ ያበረታቷቸው። ከተማሪዎች የሚቀርበውን ምላሽ በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው። ከተማሪዎቹም በሚከተለው መልኩ ምላሽ ይጠበቃል።

1. ሐ
2. ለ
3. ለ
4. ሀ

5. በመጀመሪያ ተማሪዎች “ከዚህ ታሪክ ውስጥ ያስደሰተህ/ሽን ነገር ተናገር/ሪ፡፡” ለሚለው ጥያቄ ሀሳብ እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ቃልኪዳን መጠበቁ ትልቅ ጥቅም እንዳለውና ቀበሮውም ቃል በማፍረሱና ታማኝነትን በማጉደሉ የደረስበትን አስረዷቸው፡፡
6. ከዚህ ታሪክ ምን ተማሪክ/ሽ? ለሚለው ተማሪቹ የተለያዩ አስተያየቶችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ይሁንና ቃል አለመፈጸም ስህተት እንደሆነና መልሶ ራስን ሊጎዳ እንደሚችል መረዳት እንዳለባቸው ያስገንዝቧቸው፡፡

## ትምህርት 4. መስረቅና ማጭበርበርን መጥላት

### ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

- መስረቅ እና ማጭበርበር የሚያስከትለውን ጉዳት ይለያሉ፡፡

መምህር/ት የትምህርት ይዘቱን ከማቅረብዎ በፊት ለቅድመ ግንዛቤ የቀረበውን ጥያቄ በማቅረብ ያወያዩዋቸው፡፡ በመቀጠል ማስታወሻውን አንድ ጊዜ ለተማሪዎች በማንበብ ተማሪዎቹም ደጋግመው እንዲያነቡ ይዘዟቸው፡፡ ማስታወሻውንም በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያበረታቷቸው፡፡

### ማስታወሻ

ሌብነት እና ማታለል አፀያፊ ድርጊቶች ናቸው፡፡ በህብረተሰባችን ዘንድም ተቀባይነት የላቸውም፡፡ ስለዚህ የሰው ሀቅ መስረቅ እና ማጭበርበር ትክክል አይደለም፡፡ የሰው ነገር የሚሰርቅ እርጉም ነው፣ የተረገመ ደግሞ አይሳካለትም፡፡ በተጨማሪም አታላይ ሰው አይታመንም፣ በሌላ አነጋገር ስርቆት እና ማታለል በሰዎች ዘንድ እምነት እንድናጣ ያደርጋሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን "መስረቅና ማታለል ምን ጉዳት አለው?" የሚለውን ጥያቄ ይጠይቁ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ ሐሳባቸውን ለክፍል እንድያቀርቡ ያድርጉና መልሳቸው ላይ በመመርኮዝ ሐሳብ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠልም በሠሌዳ ላይ ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡

በተጨማሪም፣ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ተግባር ለተማሪዎች በማንበብ ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡ በመጨረሻም፣ የተማሪዎችን ምላሽ መሰረት በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

በመርጃ መሳሪያነት ሌባ የሰውን ንብረት ሰርቆ ሰዎች በተለያየ ዘዴ ይዘው ለህግ ሲያቀርቡ የሚያመለክት ተንቀሳቃሽ ምስል በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ዘዴዎች በመጠቀም ለተማሪዎች ያቅርቡ፡፡

**ምዘና**

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል። እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ።

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ።
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ።
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው።

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት "በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው" በማለት ያበረታቷቸው።

**ተግባር 5.**

ከተራ ቁጥር 1-5 ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ በባዶ ቦታው ላይ እንዲያስገቡ ይዘዟቸው። መልሶቻቸውንም በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው።

1. ለ
2. ሀ
3. ለ
4. ሀ

5. ለ

6.

**የክለሳ ጥያቄ**

| I.1. እውነት/ውሸት | | II. ምርጫ |
|---|---|---|
| 1. | ውሸት | 1. ሐ |
| 2. | እውነት | 2. መ |
| 3. | እውነት | 3. መ |
| 4. | ውሸት | 4. ሀ |

# ምዕራፍ ሶስት
# ፍትህ

**(ክፍለጊዜ 20)**

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ይዘቶች አሉ፡፡ እነሱም፣ የፍትህና ፍትሃዊነት ምንነት ናቸው፡፡ ለሁለቱም ትምህርቶች በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ አጫጭር ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ ታሪኮችን በመጠቀም ፍትህ እና ፍትሃዊነት ምን እንደሆኑ እና አስፈላጊነታቸው በሰፊው ቀርቧል፡፡ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተገነዘቡ ለማወቅ የሚያስችሉ ይዘቶቹን መሰረት በማድረግ የተለያዩ የተግባር ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

**የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች**

- የፍትህና ፍትሃዊነት ምንነት ይገልጻሉ፣
- የፍትህና ፍትሃዊነት አስፈላጊነት ይናገራሉ፣
- በፍትህ እጦት ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ይለያሉ፡፡

## ትምህርት 1. የፍትህ ምንነት

- ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

የፍትህን ምንነት ከመግለጽዎ በፊት “የራስ ያልሆነን ነገር ከመሬት ብታገኝ/ኚ ምን ታደርጋለህ/ሽ?” የሚለውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ጥያቄ በማቅረብ ያወያዩዋቸው፡፡ ለተማሪዎቹም ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ በማስከተል ፍትህን መሰረት በማድረግ የቀረበውን ማስታወሻ ከተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ያንብቡላቸው፡፡ ተማሪዎቹም ደጋግመው በማንበብ በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ይዘዟቸው፡፡

በመቀጠል ሶስቱ ጓደኞች በሚል ርዕስ የቀረበውን ታሪክ መሰረት በማድረግ የቀረበላቸውን የተግባር ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡ በመቀጠል አለሙና ዋሪዮ በሚል ርዕስ የቀረበውን ታሪክ በማንበብ ማስታወሻውን መሰረት በማድረግ የቀረበውን የተግባር ጥያቄዎችን ያሰሯቸው፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን "የራስ ያልሆነን ነገር ከመሬት ብታገኝ/ኚ ምን ታደርጋለህ/ሽ?" የሚለውን ጥያቄ ይጠይቋቸው፡፡ የተማሪዎችን መልስ መሰረት በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ በመቀጠል የሦስቱን ጓደኞች ታሪክ ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የተግባር ጥያቄዎች ለተማሪዎች ያንብቡና መልሶቻቸውን ይቀበሏቸውና ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

## ምዘና

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ፡፡
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው፡፡

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ፡፡ ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት "በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው" በማለት ያበረታቷቸው፡፡

**ተግባር 1.**

1. ለ
2. ሀ
3. ሀ
4. ከዚህ ታሪክ ምን ተማሪክ/ሽ? ለሚለው ጥያቄ ተማሪዎች የተለያዩ ሐሳቦችን ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በተማሪዎቹ ሐሳብ ላይ በመመስረት ተገቢውን ማስተካከያ ይስጧቸው፡፡

ከዚህ በታች የተመለከተው የአለሙንና ዋሪዮን ታሪክ መሰረት በማድረግ የቀረበ የተግባር ጥያቄ ነው፡፡

**ተግባር 2.**

1. ሀ
2. ለ
3. ሀ
4. ይህ ታሪክ አለሙና ዋሪዮ ከመሬት ባገኙት ገንዘብ ላይ እንደ ተጣሉና ገነሜ ጠርታቸው እንደ መከረቻቸው ይናገራል፡፡ ልጆቹም የገነሜን ምክር ሰምተው ገንዘቡን ለባለቤቱ እንደመለሱ ይገልጻል፡፡ ባለገንዘቡም በተደረገው ድርግት ተደስተው ስሚቸው እና መረቋቸው እንደሄደ ያሳያሳል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹም የአለሙንና ዋሪዮን ድርጊት አድንቀው በህይወት ልምዳቸው ውስጥ እንዲያዳብሩ ይምከሯቸው፡፡

## ትምህርት 2. ፍትሃዊነት

### ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት

- የፍትሃዊነትን ምንነት ይለያሉ፡፡

የፍትሃዊነት ምንነት ከመግለጽዎ በፊት “ሁሉንም ሰው እኩል ማክበር አግባብ ነው? ለምን?” የሚለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ጥያቄ በማቅረብ ያወያዩዋቸው፡፡ የተማሪዎቹን መልስ መሰረት በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ በማስከተል በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ማስታወሻ አንድ ጊዜ ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ በተደጋጋሚ እንዲያነቡ ያበረታቷቸው፡፡ በመጨረሻም ማስታወሻውን በደብተራቸው ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን “ሁሉንም ሰው እኩል ማክበር አግባብ ነው? ለምን?” የሚለውን የግንዛቤ ጥያቄ ይጠይቁ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎቹ ጥያቄው ላይ እንዲመካከሩና የተረዱትን ደግሞ ለሌሎች እንዲያካፍሉ ያድርጉ፡፡ ከዚየም አጭር ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡ በተጨማሪም፣ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን ተግባር ለተማሪዎች አንብበው ምን እንደተረዱ ይጠይቋቸው፡፡

መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በዚህ ትምህርት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው።

በመርጃ መሳሪያነት በመንግስትም ሆነ በግል ተቋማት ውስጥ ሰዎችን በተለያዩ ምክንያቶች ሳያበላልጡ በእኩል ሲያስተናግዷቸው ወይም ሳያስተናግዱ ሲቀሩ የሚያመለክቱ ምስልሎችን፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በመጠቀም ትምህርቱን ተጨባጭ ያድርጉ።

## ምዘና

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል። እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ።

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊ አስተያየት ይስጡ።
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ።
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው።

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት “በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው” በማለት ያበረታቷቸው።

## ተግባር 3.

1. እውነት 2. እውነት 3. ውሸት

**የክለሳ ጥያቄዎች**

| እውነት ወይም ውሸት | | II. ምርጫ |
|---|---|---|
| 1. | እውነት | 1. መ |
| 2. | እውነት | 2. መ |
| 3. | እውነት | 3. ለ |
| 4. | ውሸት | 4. መ |
| 5. | እውነት | |

# ምዕራፍ አራት

# መልካም ማህበራዊ ግንኙነት

(ክፍለጊዜ 19)

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ሐሳቦች አሉ። እነሱም ጓደኝነት፣ መረዳዳትና መልካም ግንኙትን የሚጎዱ ድርጊቶች ናቸው። ለሁሉም ትምህርቶች በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ አጫጭር ማብራሪዎች ቀርበዋል። በተጨማሪም በተማሪ መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ ባህላዊ የልጆች ጫዋታና አጫጭር ታሪኮችን በመጠቀም ጓደኝነት፣ መረዳዳት እና መልካም ግንኙነት በሰፊው ተብራርተዋል።

**የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-**

- የመልካም ግንኙነትን ምንነት ይገልፃሉ፣
- መልካም ግንኙነቶችን ሊያጎለብቱ የሚችሉ ነገሮችን ይለያሉ፣
- መልካም ግንኙነትን የሚጎዱ ነገሮችን ይለያሉ።

## ትምህርት 1. ጓደኝነት

### ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት

- ጓደኝነት የሚገለፅባቸውን መንገዶችን ይለያሉ፣

መምህር/ት በዚህ ትምህርት ስር የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ለማነቃቃት ይረዳሉ የተባሉ የግንዛቤ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ በነዚህ ጥያቄዎች ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ የየቡድኖቹን ሀሳብ በተወካያቸው አማካይነት እንዲገልጹ ያበረታቱ፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ ከዚህ በታች የቀረበው ማስታወሻ በተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ሀሳብ የሚያጎለብት ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ማስታወሻ እንደ ተጨማሪ ግብዐት በመጠቀም ይግለጹላቸው፡፡

**ማስታወሻ**

ጓደኛ ማለት በዕድሜ እኩል ወይም የሚቀራረቡ ሰዎች መካከል ያለ ወዳጅነትን የሚያመለክት ነው፡፡ ጓደኛ የሆኑ ሰዎችም በመከባበር፣ በፍቅርና በአንድነት አብረው ሲጫወቱና ሲሰሩ ጓደኝነታቸው ይዳብራል፡፡ በጓደኞች መልካም ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ወደ ጠንካራ ማህበራዊ ግንኙነት ያመራል፡፡ ጓደኝነት የእርስ በርስ ግንኙነት በማጠናከር ረገድ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ስለዚህ የጓደኞችን ምክር መስማትና መከባበር አስፈላጊ ነው፡፡

ጥሩ ጓደኝነት ለመፍጠር የሚያስፈልጉ ነገሮች

- የጋራ ፍላጎትና ሐሳብ እንዳለን መለየት
- መከባበርና ለእርስ በርስ ጥቅም መቆም
- በንግግርና በመወያያ ጊዜ ደስተኛ ሆኖ መቅረብ
- ለጓደኛ እንክብካቤና ጥበቃ ማድረግ

ይሁንና ሁሉም ሰው መልካም ማህበራዊ ግንኙነትን ለመፍጠር የሚያስችሉ ተመሳሳይ ግንዛቤና ችሎታ የለንም፡፡ ጥሩ ጓደኝነትና ማህበራዊ ግንኙነት እንዲኖረን የሚያደርጉ ነገሮች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል፦

- ሠላምታ መጠያየቅ
- በጥሩ ፊት ሰውን መቀበል
- ከሌሎች ጋር አንድነት መፍጠር
- ያለንን ማካፈል
- የተቸገረውን መርዳትና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያሉትን የግንዛቤ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በቡድን እንዲወያዩበት ያድርጉ፡፡ ከዚያ በኋላ ጓደኝነትን የሚያሳይ የልጆች ጨዋታ ያንብቡላቸው፡፡ ይህንኑ ጨዋታ ተማሪዎቹ ሁለት በሁለት እንዲጫወቱ ያድርጉ፣ ጨወታው ጓደኝነትን ለማጠናከር የሚሰጠውን ጥቅም እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡ እርሶዎም

ጫወታው ለጓደኝነት መጠናከር ያለውን አስተዋጽዖ ይግለጹላቸው፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ ጓደኝነት ምን እንደሆነ እና በተማሪ መጽሐፍ ላይ የተሰጠውን ሥዕል በማየት ጓደኝነት ሊገለጽባቸው የሚችሉ መንገዶችን ያስረዱ፡፡ በመቀጠልም አጭር ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም፣ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በዚህ ትምህርት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

በመርጃ መሳሪያነት ልጆች ከጓደኞቻቸው ጋር በትምህርት ቤትም ይሁን ከትምህርት ቤት ውጭ በጥንድም ይሁን በቡድን ሲጫወቱ የሚያመለክቱ ምስሎች ወይም ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በማቅረብ ትምህርቱን ተጨባጭ ያድርጉ፡፡

**ምዘና**

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ፡፡
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው፡፡

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት “በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው” በማለት ያበረታቷቸው።

**ተግባር 1.**

1. ሀ
2. ሀ
3. መ
4. ለ4ኛ ጥያቄ መልስ ተማሪዎች የተለያዩ ሐሳቦችን ሊሰጡ ይችላሉ። በተማሪው መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን ምስል በመመልከት ምን እንደተረዱ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ያድርጉ። በመጨረሻም ጓደኝነት ምን እንደሆነና ጥቅሙን ያስረዷቸው።

## ትምህርት 2. መረዳዳት

**ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት**

- መረዳዳት ግንኙነትን ከሚያጠናክሩ ነገሮች አንዱ እንደሆነ ይረዳሉ፣

መረዳዳት በሚል ርዕስ የቀረበውን የትምህርት ይዘት ከማቅረብዎ በፊት የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ለማነቃቃት ለግንዛቤ የቀረቡትን ጥያቄዎች በማቅረብ ያወያዩዋቸው፡፡ በሚሰጡት መልስ ላይ ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያለውን የግንዛቤ ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች ምን በመሥራት ወላጆቻውን እነደሚረዱ በመጠየቅ ሐሳባቸውን ከተቀበሉ በኋላ የማጠቃለያ ሐሳብ ይስጧቸው፡፡ ከዚያም መጽሐፋቸው ላይ ያለውን ምስል መሰረት በማድረግ ምስሉ ስለምን እንደሚያስገነዝብ ግምታቸውን

እንዲሰጡ ያድርጉ፡፡ ተማሪዎች ተረዳድተው ምን እየሠሩ እንደሆነም ይጠይቋቸው፡፡

በተጨማሪም፣ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የተግባር ጥያቄዎች ለተማሪዎች ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያም ለጥያቄዎቹ የሚሰጡትን መልሶች በመቀበል ተገቢውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

በተማሪው መጽሃፍ ላይ ያለውን የዐዞ እና የሶስቱ ወንድማማቾች ታሪክ ያንብቡላቸው፡፡ በቀረቡት ምስሎች ላይም የተረዱትን እርስ በራሳቸው ይነጋገሩበት፡፡ በመጨረሻም፣ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በዚህ ትምህርት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

በመርጃ መሳሪያነት የአዞን ምስል በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች በመጠቀም ለተማሪዎችዎ ያሳዩዋቸው፡፡

**ምዘና**

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ፡፡
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው፡፡

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ፡፡ ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት “በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው” በማለት ያበረታቷቸው፡፡

**ተግባር 2.**

1. ሀ
2. መ
3. ሦስቱም ወንድማማቾች የተለያየ ችሎታ ስላላቸው እህታቸውን በማትረፍ ሂደት ውስጥ ጠቅሟቸዋል፡፡ ሁላቸውም እህታቸውን በማትረፍ ሂደት ውስጥ የተቻላቸውን ሁሉ በመረዳዳት ከሞት እንዳተረፏት ይንገሯቸው፡፡ ታሪኩም መረዳዳት መልካም እንደሆነና ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚጠቅም ያስረዷቸው፡፡
4. የዚህ ጥያቄ መልስ የተለያየ ሊሆን ስለሚችል የሁሉንም ተማሪዎች ሐሳብ ይቀበሉ፡፡ ለተማሪዎች ተገቢውን ግረመልስ በመስጠት በሚከተለው ሀሳብ መረዳዳትን የሚያጠናክር ሀሳብ ይግለጹላቸው፡፡ በማህበራዊ ግንኙነት ውስጥ መተባበር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የተለያዩ ሰዎች ተለያየ ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ በትብብር ቢሠራ ወደ አንድ ግብ ያደርሳል፡፡ መተባበር ጥሩ የማህበራዊ ግንኙነት ለመፍጠር ይረዳል፡፡

## ትምህርት 3. ጓደኝነትን የሚጎዱ ነገሮች

### ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት

- ጓደኝነትን የሚጎዱ ነገሮችን ይዘረዝራሉ፡፡

መምህር/ት የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ለማነቃቃት የቀረበውን የግንዛቤ ጥያቄ በማቅረብ ለሚቀጥለው ትምህርት ይዘት ያዘጋጇቸው፡፡

### ማስታወሻ

መልካም ማህበራዊ ግንኙነቶችን የሚጎዱ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ከእነርሱም ጥቂቶቹ ከቤተሰብ ወይም ካደግንበት ማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ የሚመጡ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ከግል ባህሪያችን ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አለመከባበር፣ አንድነት ማጣት፣ንፉግ መሆን፣ ከሌላ ሰው ጋር ለመሥራት ፍላጎት ማጣት፣ የበላይነት ማሳየት፣ መፍራት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

መምህር/ት፣ መጀመሪያ በተማሪው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን “ከጓደኞችህ/ሽ ጋር ተጣልተህ/ሽ ታውቃለህ/ቂያለሽ? ለምን?” የሚለውን ጥያቄ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከተወያዩ በኋላ ሐሳባቸውን ለክፍሉ አንዲያቀርቡ ያበረታቱ፡፡ ከዚያም ተማሪዎቹ ባነሱት ሀሳብ ላይ ማስተካከያ በመስጠት ለሚቀጥለው ትምህርት ያዘጋጇቸው፡፡  በመቀጠልም ጓደኝነትን ሊጎዱ የሚችሉ ምን ምን

እንደሆኑ የቀረቡትን ነጥቦች ከተማሪው መጽሀፍ ላይ አጭር ማስታወሻ ይስጧቸው፡፡

ስለተማሪ ጃራና ጓደኛው ታሪክ ከመማሪያ መጽሐፉ ላይ ድምፅ ከፍ በማድረግ ያንብቡላቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ተማሪዎቹ ስለ ጃራ ድርጊት “ልክ ነው፤ ልክ አይደለም” ብለው በቡድን ይወያዩበት፡፡ ጃራ የጓደኛውን ብዕር በመስረቁና የጓደኛውን መጽሐፍ በመቅደዱ ምክንያት ጓደኛ አጥቶ ብቻውን እንደቀረ ይንገሯቸው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት ከግብረገብ ውጭ መሆኑንና መልካም ግንኙነትንም እንደሚጎዳ ያስረዷቸው፡፡ በመጨረሻም፣ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ በዚህ ትምህርት ስር ያሉትን ጥያቄዎች ያሰሯቸው፡፡

በመርጃ መሳሪያነት ልጆች በተለያዩ ምክንያቶች ከጓደኞቻቸው ጋር ሲጣሉ የሚያመለክቱ ምስሎችን በማቅረብ ተማሪዎቹ በተጨባጭ ትምህርቱን እንዲከታተሉ ያድርጉ፡፡

**ምዘና**

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ፡፡

- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው።

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት "በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው" በማለት ያበረታቷቸው።

**ተግባር 3.**

1. በመጥፎ ባህይሪው ምክንያት
2. ትክክል አይደለም። ምክንያቱም የጓደኛን ንብረት መስረቅ ከጓደኛ ጋር ያጣላል። መስረቅ ከግብረገብ ውጭ መሆን ያመለክታል።
3. መ

**የክለሳ ጥያቄዎች**

| I. እውነት ወይም ውሸት | | II. ምርጫ | |
|---|---|---|---|
| 1 | ውሸት | 1 | መ |
| 2 | እውነት | 2 | ሐ |
| 3 | እውነት | 3 | መ |

# ምዕራፍ አምስት

## ለጋራ ንብረት መጠንቀቅ

### የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች

(ክፍለጊዜ 20)

- የጋራ  ንብረትን ምንነት ይገልጻሉ፤
- የጋራ ንብረትን ይለያሉ፤
- የጋራ ንብረት ቅድምያ ይሰጣሉ፤
- የጋራ ጥቅም እንቅፋቶች ይለያሉ።

### ትምህርት 1. የጋራ ንብረት

### ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት

- የጋራ  ንብረት የሆኑ ነገሮችን ይለያሉ።

### የግንዛቤ ጥያቄ

አንድ ማህበረሰብ በጋራ የሚጠቀምባቸውን ነገሮች ይዘረዝራሉ።

መምህር/ት የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ለማነቃቃት የቀረበውን የግንዛቤ ጥያቄ በማቅረብ ለሚቀጥለው ትምህርት ይዘት ያዘጋጇቸው። ከተማሪዎቹ የሰበሰቡትን መልስ ተገቢውን ግብረመልስ በማከል ያጠናክሩ።

### ማስታወሻ

የጋራ ንብረት ማለት የሰው ልጅ ሁሉ ሊጠቀምባቸው የሚችል

የጋራ መገልገያ ሀብት ማለት ነው። እነዚህም ንብረቶች እንደ ውሃ፣ መንገድ፣ ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤት፣ የስፖርት ሜዳ፣ የህዝብ መጸዳጃ ቤት፣ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል።

ስለ የጋራ ንብረት ከማስተማርዎ በፊት ተማሪዎች በቤታቸው ውስጥ ስለሚጠቀሙበት መሳሪያዎች የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያድርጉ። በመቀጠል የሚጠቀሙበት መሳሪያ የግላቸው ወይም የጋራ ስለመሆኑ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው።

በተጨማሪም በአከባቢያቸው ከጓደኞቻቸው ጋር በጋራ የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ካሉ ምን ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። የተማሪዎቹን መልሶች ካዳመጡ በኋላ ለተማሪዎች ግብረመልስ ይስጧቸው።

ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ላይ የሚገኘውን ምስል በሚገባ ተመልክተው ምን እንደተረዱ በተግባር 1 ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ። ከተማሪዎቹ የሚገኘው መልስ የሚከተሉት ሊሆኑ እንዲችሉ ማጤን ያስፈልጋል።

**ተግባር 1.**

1. ውሃ፣ ሆስፒታል፣ መንገድ፣ ትምህርት ቤት
2. ውሃ እየቀዳ፣አቅጣጫ ጠቋሚ ወይም መረጃሰጭ ጽሁፍ የሚያነብ ተማሪ

## ትምህርት 2. ውሃ

**ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃቶች**

- ውሃ የጋራ ሀብት መሆኑን ይናገራሉ፡፡
- የውሃን ንጽህና መጠበቅ የማን ድርሻ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የውሃን ንጽህና መጠበቅ የማን ድርሻ ነው?

መምህር/ት የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ለማነቃቃት የቀረበውን የግንዛቤ ጥያቄ "የውሃን ንጽህና መጠበቅ የማን ድርሻ ነው?" በማቅረብ ለሚቀጥለው ትምህርት ይዘት ያዘጋጇቸው፡፡

**ማስታወሻ**

ከዚህ በታች የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት ያደረገ ትምህርት ከማቅረብህ/ሽ በፊት ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ውስጥ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ ከተወያዩ በኋላ ጽብረቃ እንዲያቀርቡ ከተወሰኑ ቡድኖች ሀሳብ በመቀበል ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

ውሃ አንድ ማህበረሰብ በጋራ ከሚጠቀምበት ንብረት ውስጥ ይመደባል፡፡ ንጹህ ውሃ ለመጠጥ፣ ለግል ንጽህና አጠባበቅ እና ልብሳችንን ለማጠብ ያገለግላል፡፡ ዕጽዋት እና እንስሳትም ለመጠጥ ይጠቀሙበታል፡፡ ስለዚህ ስንጠቀምበት ማባክን የለብንም፡፡ የውሃን ምንጭ ማድረቅ፣ ቆሻሻን በውስጡ መድፋት እና ከፍቶ በመተው ያለ አግባብ ማባከን ግብረገብነትን ማጣት

ነው። ኦሮሞ ለውሃ ምንጭ ካለው ክብር የተነሳ በውሃ ዳር የሚበቅሉትን ቡቃያዎች አይቆርጥም። ውሃን ሲሻገር ለውሃም በመሳሳት ይጠነቀቅለታል።

**ተግባር 2.**

ይህንን ተግባር ተማሪዎች በግላቸው እንዲሰሩ ያድርጉ። ተማሪዎች በሚሰጡት መልስ ላይ በመመርኮዝ አጭር ግብረመልስ ይስጧቸው። ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው መልስ የሚከተሉት እንደሆኑ ይከታተሉ።

1. ውሸት
2. እውነት
3. ውሸት
4. መ

## ትምህርት 3. ትምህርት ቤት

### ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት

- ትምህርት ቤት የጋራ ንብረት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ትምህርት ቤት የግል ንብረት ነው? ወይስ የጋራ ንብረት ነው?

ይህንን ትምህርት ከማቅረብህ/ሽ በፊት ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ውስጥ በቀረበው የግንዛቤ ጥያቄ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በመቀጠል ከተወሰኑት ቡድኖች ሀሳብ በመቀበል በትምህርት ቤታቸው ያለውን ንብረት እና አጠቃቀሙን በተመለከተ አጭር ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡

**ማስታወሻ**

ትምህርት ቤት ማንኛውም ሰው ዕውቀት የሚያገኝበት ቦታ ነው፡፡ የምሁራን ምንጭም ነው፡፡ የደስታና በፍቅር የሚጫወቱበት ቦታ ሆኖም እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህ የትምህርት ቤት ንብረት የጋራ ንብረታችን ስለሆነ መንከባከብ እና በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ መጸዳጃ ቤት ስንሄድ፣ እጃችንን ስንታጠብ፣ ጥቁር ሰሌዳችን ላይ ስንጽፍ፣ ወንበራችንን እና ጠረጴዛዎችን ስንጠቀም በአግባቡ ሳናበላሽ መጠቀም ይኖርብናል፡፡

በመጨረሻም ትምህርት ቤቴ በሚል ርዕስ የቀረበውን መዝሙር በቡድን እንዲዘምሩ ያድርጉ፡፡ የመዝሙሩንም መልዕክት ይንገሯቸው፡፡

**ተግባር 3:**

ይህንን ተግባር ተማሪዎች በግል እንዲሰሩ ያድርጉ፡፡በመቀጠል የሚሰጡትን መልስ በመመልከት ግብርመልስ ይስጧቸው፡፡

1. ሀ
2. ሀ
3. መ
4. መ

## ትምህርት 4. መንገድ

**ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት**

- መንገድ የጋራ ንብረት መሆኑን ይገልጻሉ።

**የግንዛቤ ጥያቄ**

መንገድ የጋራ ንብረት ነው? ለምን?

**ማስታወሻ**

በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረበውን የግንዛቤ ጥያቄ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው እንዲመልሱ ያድርጉ። ተማሪዎች በሚወያዩበት ግዜ እያንዳንዱን ቡድን በመጎብኘት ድጋፍ ለሚፈልጉ አስፈላጊ ድጋፍ ያድርጉላቸው። በተጨማሪም በመጽሐፋቸው ላይ የሚገኘውን ምስል በመመልከት ምን እንደተረዱ እንዲናገሩ ያድርጉ። በመንገድ የሚጠቀሙ እነማን እንደሆኑ (ለምሳሌ፡ መኪና፣ በቁሎ፣ ፈረስ፣ ከብት፣ ሰው እና የመሳሰሉት) እንዲናገሩ ያድርጉ። መንገድ ስያቋርጡም ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው ይንገሯቸው። በመጨረሻም በሚያቀርቡት ሀሳብ ላይ ግብረመልስ ይስጧቸው።

**ተግባር 4**

ይህ ተማሪዎች በግል የሚያከናውኑት ተግባር ነው። ጥያቄዎቹን በደብተራቸው ላይ በመገልበጥ እንዲሰሩ ያድርጉ።መልሶቹም የሚከተሉት እንደሆኑ ይከታተሉ።

1. ሀ
2. መ

3. መ

**ምዘና**

በዚህ ትምህርት ስር የተለያዩ የግምገማ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እርስዎም ተከታታይ ምዘናዎችን፣ ጥያቄዎችን እና ክትትልን ሲያደርጉ ከዚህ በታች ያሉትን ነጥቦች መጠቀም ይችላሉ፡፡

- ተማሪዎች የክፍል ሥራ ሲሰሩ ይቆጣጠሩና አስፈላጊውን ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡
- የተማሪዎችን ብቃትና ችሎታ ይመዝግቡ፡፡
- የተለያዩ የክፍልና የቤት ስራዎችን ይስጧቸው፡፡

በተማሪዎች ሥራ ላይ ገንቢ አስተያየት ይስጡ፡፡ ለምሳሌ፣ ተማሪዎች ጥያቄ ሲመልሱ ስም በመጥራት “በጣም ጥሩ ነው፣የተሻለ ነው” በማለት ያበረታቷቸው፡፡

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1. እውነት
2. ውሸት
3. ውሸት
4. እውነት
5. እውነት

**መመሪያ II፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጥ/ጪ፡፡**

1. መ
2. ለ
3. መ
4. መ
5. መ

# ምዕራፍ ስድስት: ባህላዊ ቅርሶች

**የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች** **(ክፍለጊዜ 20)**

- ባህላዊ ቅርሶች ምን እንደሆኑ መናገር፤
- የተለያዩ ባህላዊ ቅርሶችን መለየት፤
- ባህላዊ ቅርሶችን መንከባከብ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት፤
- ለባህላዊ ቅርሶቸ የሚደረጉትን እንክብካቤዎች መለየት ናቸው፡፡

## ትምህርት 1: የባህላዊ ቅርሶች ምንነት

- **ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት**
  - ባህላዊ ቅርሶች የሆኑትን ይዘረዝራሉ፡፡

መምህር/ት በዚህ ትምህርት ስር የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ለማነቃቃት ይረዳል ተብሎ የታሰበ ባህል ማለት ምን ማለት ነው? የሚል ጥያቄ ቀርቧል፡፡ በዚህ ጥያቄ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ የየቡድኖቹን ሀሳብ በተወካዮቻቸው አማካይነት እንዲገልጹ ያግዙአቸው፡፡ ተገቢውንም ግብረመልስ ይስጧቸው፡፡ በተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ ላይ የቀረበውን የባህልን ምንነት የሚገልጽ ማስታወሻ ያነብቡላቸው፤ ተማሪዎቹም በደብታራቸው ላይ እእንዲጽፉ ይንገሯቸው፡፡

***ማስታወሻ***

*በተማሪ መጽሐፍ ላይ በቀረቡትን ጥያቄዎች ላይ ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው እንዲመልሱ ያድርጉ፡፡ ስለ ባህላዊ ዕቃዎች እና ታሪካዊ ቦታዎች የሚያውቁትን ነገር እንዲነጋገሩ ያድርጉ፡፡*ተማሪዎች በሚወያዩበት ጊዜ እያንዳንዱን ቡድን በመጎብኘት አስፈላጊ ድጋፍ ያድርግሉኋቸው፡፡ በተማሪ መዕሐፍ ላይ የሚገኘውን ስለ ባህላዊ ቅርሶች ማለትም የድሮ ዕቃዎች፣ ልብሶች፣ የተፈጥሮ ዋሻዎች፣

ጥንታዊ ግንቦች እና ባህላዊ ምግቦችን በመጥቀስ የቀረበውን ገለጻ በማየት ማብራሪያ መስጠት ይቻላል።

**ተግባር 1**

በመጀመሪያ ተማሪዎቹ በመጽሐፋቸው ላይ የቀረበላቸውን ምስል በደንብ እንዲመለከቱ ያድርጉ። ስለተመለከቱት ምስልም የተረዱትን ነገር ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ተማሪዎች የሚያውቁትን ታሪካዊ ቦታዎች፣ የባህል ዕቃዎች፣ የባህል ምግቦች፣ የባህል ዘፈኖች እንዲናገሩ ያበረታቷቸው።

በምስል ላይ የምናያቸው ነገሮች ሁሉ ባህላዊ ቅርሶች እንደሆኑ አስረዷቸው።

**"ባህል"** የሚለው ቃል ብዙ ትርጉሞች ቢኖረውም ዕውቀት፣ እምነት፣ አርት፣ ግብረገብ፣ ሕግ እና የአንድን አከባቢ ማህበረሰብ ልማዶች የሚያካትት ነው።

- ✓ ባህል የግል ንብረት አይደለም
- ✓ ባህል የአኗኗር ሁኔታን እና የተወሰኑ ቡድኖች ያላቸውን የጋራ ጠባይ የሚያመለክት ነው።
- ✓ ባህል የአንድን ማህበረሰብ ዕውቀት፣ እምነት፣ አመለካከት፣ ሕግ፣ ጠባይ እና ችሎታን የሚያጸንባርቅ ነው።

**"ቅርስ"** ማለት ደግሞ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ሆነው ከአንድ ትውልድ ወደ ሌላው የሚተላለፉ ነገሮች ማለት ነው። ስለዚህ ባህላዊ ቅርሶች የቀድሞ የሰው

ልጆችን ታሪክ የአሁን እና ወደፊት የሚመጣን  የሚያገናኝ ነው፡፡

ባህላዊ ቅርሶች፤ ግብረገብ፣ እምነት፣ ዕውቀት፣ ችሎታ እና የማህበረሰቡን እሴት ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለውን ነገር የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ ስለዚህ ቅርስ የቀድሞ ሰው የተጠራቀመ ልምድ ተብሎ ይጠራል፡፡

ተግባር 2

መምህር/ት፤ ተግባር 2ን ተማሪዎቹ በየግላቸው በደበተራቸው ላይ  እንዲሰሩ ይንገሩአቸው፡፡ መስራታቸውንም ደብተሮቻቸውን ዞረው በማየት ያረጋግጡ፡፡ ለመልሶቻቸውም መጋቤ ምላሽ ይስጡቸው፡፡

<u>መልስ</u>

1. ሀ
2. ሀ
3. መ
4. መ
5. መ

የተለያዩ በአሎችን አከባበርን የሚያውቁ ሁለት ተማሪዎች እንዲጠያየቁ አድርጉ፡፡ የአከባበሩም ሁኔታ ተመሳሳይ ወይም የተለያየ መሆኑን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ በተማሪዎች መጽሐፍ ላይ ያለውን ምስል ላይ በመመስረት የተለያዩ የባህል ልብስ፣ ምግብ እና መጠጥ፣ ባህላዊ ዘፈኖች መኖራቸውን እና ልዩነት ያላቸው

መሆኑን ገለጻ ያድርጉላቸው። ለምሳሌ፡ በእሬቻ በአል አከባበር ወቅት የባህል ልብስ በመልበስ እየዘፈኑ ወደ መልካ/ ተራራ ይኬዳል።

በአጠቃላይ ባህላዊ ቅርሶች የሚባሉት ከ ትውልድ ወደ ትውልድ በሚተላለፈው ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ክብረበዐላት አከባበር፣ የአንድ ማህበረሰብ የባህል ልብስ፣ የምግብ እና መጠጥ ሁኔታ፣ የታሪካዊ ሕንጻዎች ግንባታ ሁኔታ እና የማህበረሰቡ ልማዶችን የሚያጠቃልል ይሆናል።

## ትምህርት 2: የባህላዊ ቅርሶች ዓይነቶች

**ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት**

- የባህላዊ ቅርሶችን ዓይነቶች ይናገራሉ፤

**ማስታወሻ**

*የምዕራፉን ትምህርት ከግብ ለማድረስ በመጀመሪያ ተማሪዎች በተማሪ መጽሐፍ ላይ "በአከባቢህ/ሽ ያሉ ባህላዊ ቅርሶች ዘርዝር/ሪ?"የሚለውን ጥያቄ በቡድን እንዲሰሩ ያግዟቸው:: ይህም በትምህርቱ ላይ አስቀድመው ያላቸውን እውቀት ለመረዳት እና ለማወቅ ያግዛል:: በመቀጠልም ለመልሶቻቸው ግብረመልስ ይስጧቸው:: ተማሪዎች በግል በተማሪ መጽሐፍ ላይ የሚገኘውን ምስል ከተሰጠው ገለጻ ጋር እንዲያዛምዱ ይምሯቸው::ይህም ተማሪዎች ስለ ባህላዊ ቅርሶች ዓይነቶች እንዲያውቁ ያደርጋል:: የተማሪዎችን ስራ በመመልከት ስለ ምስሎቹ ግብረመልስ ይስጧቸው:: እንዲሁም ቀጥሎ ያሉትን ማብራሪያዎች መጠቀም ይችላሉ:: በመገኛቸው እና በአገልግሎታቸው ባህላዊ ቅርሶችን በሁለት መክፈል ይቻላል:: እነዚህም የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ተብለው ይጠራሉ::*

**የሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች**

- የሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች የሚባሉት የጥንታዊ መሳሪያዎች ቅሪት ሆነው በመልክ እና በአካል የሚታዩ ናቸው::
- በዓይናችን አይተን በእጃችን መዳሰስ የምንችላቸው ናቸው:: እነዚህም ቅርሶች የሰው ልጆች የፈጠራ ስራዎች ናቸው:: እነዚህም **የሚንቀሳቀሱ** እና **የማይንቀሳቀሱ** ባህላዊ ቅርሶች ይባላሉ::
- **የሚንቀሳቀሱ** ባህላዊ ቅርሶች ተጨባጭ የሆኑ እና ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ልናንቀሳቅሳቸው የምንችል እንደ ምስል፣ ቅርጻ ቅርጾች፣ ሳንቲሞች፣ የእጅ ጽሑፍ፣ መሳሪያዎች፣ ልብሶች፣ የቤት ዕቃዎች እና የመጓጓዣ ሁኔታዎችን ያጠቃልላል::

- **የማይንቀሳቀሱ** ባህላዊ ቅርሶች የሚባሉት ደግሞ እንደ ሐውልቶች፣ በመቃብር ላይ የሚሰሩ ሐውልቶች፣ ሕንጻዎች (መዝጊዶች፣ ቤተክርስቲያናት፣ ቤተ መንግስቶች፣ የመኖሪያ ቤቶች) እና ድልድዮችን የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህን ቅርሶች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስ አንችልም።

የሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች የሚባሉት ደግሞ የብሔራዊ ሎተሪ ወረቀቶች፣ ማህተም እና የብር ኖቶች ላይ የሚተዋወቁ ምስሎች ናቸው። ለምሳሌ በ 2013 የወጣው የኢትዮጵያ የብር ኖት የሶስት ብሔራዊ ቅርሶችን ምስል ማለትም (የአክሱም አውልት፣ የፋሲለደስ ቤተመንግስት፣ እና የጀጎል ግንብ) አለው። እንዲሁም የአባጅፋርን ቤተመንግስት፣ የኩምሳ ሞሮዳን ቤተ መንግስት እና የሶፍ ኡመርን ዋሻ ታዋቂ ከሆኑት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

**የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች**

የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች የሚባሉት የሰው ልጆች ማስታወሻ ሆነው በዓይን የማይታዩ እንደ ቋንቋ፣ እሴት፣ ባህል፣ ሙዚቃ፣ ግጥም፣ የሀይማኖታዊ በዓላት አከባበር፣ ሀገር በቀል ዕውቀት  እና የመሳሰሉትን ያካተተ ነው። እነዚህም የአኗኗር ሁኔታዎች፣ እምነት፣ ዕውቀት፣ ግብረገብ እና  የማህበረሰቡን የዕድገት ደረጃ ይገልጻሉ። ለምሳሌ በገዳ ስርዓት ውስጥ የሚከበሩ ስነስርዓቶች (የባሊ ወይም ስልጣን ርክክብ ስነስርዓት እና የእሬቻ በዓል አከባበር) የሴቶች በዓል (አቴቴ)፣ የጉማ ስርዓት፣ የጋብቻ ስርዓት፣ የዘመን መለወጫ እና የተለያዩ ሀይማኖታዊ በዓላት ናቸው።

እነዚህም የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች የማህበረሰቡን የባህል ማንነት መሰረቶች ወይም የአንድ ማህበረሰብ ማንነት የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህም በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል ያሉትን የግንዛቤ እና የባህል ልዩነቶች በመጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና አላቸው።

ተግባር 3

መምህር/ት፤ ተግባር 3ን ተማሪዎቹ በግላቸው እንዲሰሩ ያድርጉ። ለመልሶቻቸው መጋቤምላሽ ይስጧቸው፡፡

መልስ

1. መ
2. ሐ
3. የሚዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች
4. ሀ
5. የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች

## ትምህርት 3: የባህላዊ ቅርሶች ጥቅም

**ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባ የመማር ብቃት**

- የባህላዊ ቅርሶችን ጥቅም ይናገራሉ፡

**ማስታወሻ**

ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ላይ ያለውን "ባህላዊ ቅርሶች ምን ምን ጥቅሞች አሏቸው?" የሚለውን ጥያቄ በቡድን ሆነው እንዲያዩትና እንዲወያዩበት ጥቂት ደቂቃ ይስጧቸው። በቡድን ከተወያዩ በኋላ የተወሰኑ ቡድኖች ሀሳባቸውን ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ያድርጉ። ተማሪዎቹ ባቀረቡት ሀሳብ ላይ ግብረመልስ ይስጧቸው።

እሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ከሚያከብራቸው በዓላት አንዱ ነው። ይህ በአል በሁለት ይከፈላል፡- የመጀመሪያው ክረምት አልፎ መስከረም አጋማሽ የሚከበር ሆኖ የበአሉም አላማ "የክረምቱን ጨለማ አሳልፈህ የበልጉን ብርሃን ያሳየኸን አምላክ ተመስገን" በማለት ምስጋናን ለፈጣሪ ማቅረብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የበልግ ወቅት ሲገባ ወደ ተራሮች በመውጣት አምላክን በማመስገንና መጪው የክረምት ወቅት የሰላም እንዲሆን የሚለማመኑበት በአል ነው።

በተጨማሪም ቀጥሎ ያለውን አጭር መግለጫ በመጠቀም የትምህርቱን ዓላማ ማስጨበጥ ትችላለህ/ሽ። ባህላዊ ቅርሶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ብዙ ጥቅሞች አሉት።

- ባህላዊ ቅርሶቸ ታሪካችንን፣ ስልጣኔ እና የሰው ልጆችን ለውጥ ለመረዳት ተጨባጭ ማስረጃ በማቅረብ የማህበረሰባችንን ማንነት ለመገንባት በዓለም አቀፍ ደረጃችንን ለማወቅ ትልቅ ስፍራ አለው።
- ያለፈው ታሪካችን ዕውቀት ማንነታችን፣ የጋራ ሀብታችንን፣ አንድነት እና ልዩነታችንን፣ የስኬት እና የውድቀት ታሪክን ያሳያል።

- ባክላዊ ቅርሶች ለአንድ ሕዝብ እንደ የአንድነት እና ቁርኝት ምልክት ያገለግላል።
- ለሀገር ፍቅር ስሜት፣ እራስን ለማወቅ እና ለአንድነታችን ስፍራ በመስጠት ክብር እና ጥበቃ ለማድረግ ሊያነሳሳ ይችላል።
- ባህላዊ ቅርሶች በተለያዩ ባህሎች መካከል ዕውቀት እና ችሎታ ለመከፋፈል ትልቅ ዕድል ይፈጥራሉ።

## ትምህርት 4: ባህላዊ ቅርሶችን መንከባከብ

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት:

ባህላዊ ቅርሶችን ይንከባከባሉ።

### ማስታወሻ

በመጀመሪያ ደረጃ ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ላይ የሚገኙ ጥያቄዎች ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ። በመቀጠል ስለ ባህላዊ ቅርሶች እንክብካቤ ያላቸውን ዕውቀት እንዲነጋገሩ ያድርጉ። ለምሳሌ እንዳይሰበሩ በማስቀመጥ መንከባከብ፣ መጠገን እና እንዳይሰረቁ ማድርግን መጥቀስ ይቻላል።

በተጨማሪም ተማሪዎች በመጽሐፋቸው ላይ የሚገኘውን ምስል በመመልከት ባህላዊ ቅርሶችን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል እንዲረዱ አድርጓቸው።

"እንክብካቤ" የሚለው ቃል  አሁን ያለውን ነገር አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲቆይ መጠበቅን ያመለክታል። ይህም ከዚህ በፊት የነበረውን መጠን፣ ቅርጽ፣ ቀለም፣ ጠባይ እና ትርጉም ሳይለውጥ መጠበቅ ማለት ነው። ባህላዊ ቅርሶችን በመንከባከብ ከትውልድ ወደትውልድ በማስተላለፍ ውስጥ መሳተፍን ያመለክታል።

- ሕገወጥ ዘረፋ እና ንግድ እነዚህን ባህላዊ ቅርሶች በማጥፋት ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው።
- ከግንዛቤ፣ ችሎታ እና ገንዘብ እጥረት የተነሳ ባህላዊ ቅርሶችን አለመንከባከብ በጣም አደገኛ ነው።
- ጥቂት ታሪካዊ ቅርሶች እና አንድ አንድ ሀገራዊ ፓርኮችን ለሕገወጥ ሰፈራ፣ ለመሬት ወረራ፣ ለአደን፣ ለማዕድናትን  እና እንጨት ፍለጋ ይጋለጣሉ።

- ከቦታ ወደ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ባህላዊ ቅርሶችን መዝግቦ አለመያዝ ችግርም ትልቅ ውድቀት እያስከተለ ይገኛል፡፡
- እንድ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተት እና ከባድ ዝናብ ለባህላዊ ቅርሶች መመናመን ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

**የምዘና እና ግምገማ ዘዴዎች**

- ተማሪዎች የክፍል ስራ ሲሰሩ መከታተል እና ምልከታ ማድረግ፤
- የተማሪዎችን ብቃት እና ችሎታ እየመዘገቡ መሄድ፤
- የክፍል እና የቤት ስራዎችን መስጠት፤
- ተማሪዎች ጥያቄዎቹን እና ተግባራቱን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ ገንቢ ግብረመልስ መስጠት፡፡ ለምሳሌ፡
  - ✓ ተማሪዎች ምልስ ስሰጡ ጥሩ ነው፣ በጣም ጥሩነው, 'እጅግ በጣም ጥሩ ነው በማለት ማነቃቃት፤
  - ✓ ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀት፤ አስፈላጊ ሆኖ ስገኝ ደግሞ በጥንድ በማደራጀት ማሰራት፤
  - ✓ ተማሪዎችን የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ጽሑፎችን ማንበብ እና ቀድሞ ከላቸው ዕውቀት ጋር ማገናኘት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**የቃለት ትርጉም እና ቁልፍ ሀረጋት**:

- **ባህል**: ሀሳብ፣ ልማድ፣ የማህበረሰቡ ጠባይ እና የተለያዩ የሰዎች ወይም የአንድ ማህበረሰብ አኗኗር፤
- **ቅርስ**: ከተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ከሆኑ ነገሮች የሚሰሩ ሆነው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ናቸው፡፡
- **የቁሳዊ ባህላዊ ቅርሶች**: በዓይን የሚታዩ እና በእጅ የሚዳሰሱ እንዲሁም በተጨባጭ የሚታዩ ነገሮች ናቸው፡፡

- **መንፈሳዊ ባህላዊ ቅርሶች**፡ ሙዚቃ፣ የገዳ ስርዓት፣ እሴት፣ ቋንቋ እና የሀይማኖታዊ በዓላት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- **ተንቀሳቃሽ ባህላዊ ቅርሶች**፡ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ልናንቀሳቅሳቸው የምንችላቸው ቅርሶች ናቸው፡፡
- **የማይንቀሳቀሱ ባህላዊ ቅርሶች**፡ ከቦታ ቦታ የማይንቀሳቀሱ ባህላዊ ቅርሶች ማለት ነው፡፡
- **መንከባከብ**፡ መልኩን እና ተፈጥሮውን ሳይቀይር እንደመጀመርያው እንዲቆይ እንክብካቤ ማድረግ ነው፡፡

## ከምዕራፉ ውስጥ የወጡት ጥያቄዎች መልስ

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተማሪዎች እንደ የቤት ስራ እና የተሰጠ ስራ ይዘው በመግባት እንድሰሩ አድርግ፡፡ የተሰጠን ስራ በማረም ግብረመልስ ስጣቸው፡፡ ያገኙትን ነጥብ በመመዝገብ እንደ ተከታታይ ምዘና መጠቀምም ይቻላል፡፡

### የመጨረሻው ምዕራፍ መልመጃዎች መልስ

| አዛምድ | እውነት /ውሸት |
|---|---|
| 1. መ | 1. እውነት |
| 2. ሐ | 2. እውነት |
| 3. ሀ | 3. እውነት |
| 4. ለ | 4. ውሸት |
| 5. ሠ | 5. እውነት |

# የግብረገብ ትምህርት መርሃትምህርት
# ሁለተኛ ክፍል

## ምዕራፍአንድ የራስን ክብርና ደህንነትመጠበቅ

(ክፍለጊዜ 18)

### የሚጠበቁየመማርብቃቶች

- የክብርንምንነትማብራራት፤
- የክብርንአስፈላጊነት መናገር፤
- የራስን ደህንነት ማስጠበቂያ ዜዴዎችመዘርዘር፤
- ክብር እንዴት እንደሚገለጽ መለየት፤
- ጉዳትከሚያደርሱነገሮችራስንመጠበቅ::

| ቢያንስሊጎናጸፉየሚገባቸውየመማር ብቃቶች | የትምህርቱይዘት | የመማርማስተማርዘዴ | ምዘና |
| --- | --- | --- | --- |
| - የክብርንምንነትትገልፃለህ/ጭ ያሽ፤<br>- የክብርንአስፈላጊነትትገልፃለ ህ/ጭ ያሽ፤<br>- ክብርንእንዴትማሳየትእንደ ሚቻልትናገራለህ/ሽ::<br>- የክብርአሰጣጥማኅልበቻመንገ ዶችንትለያለህ/ሽ::<br>- ደህንነታችንላይጉዳትሊያደር ሱየሚችሉነገሮችንትዘረዝራ ለህ/ሽ::<br>- ደህንነታችንንየምንጠብቅባቸ | 1. ክብር<br>2. የክብርአስፈላጊ ነት<br>3. ክብርንማሳያና ማሳደጊያመንገ ዶች<br>4. የራስንደህንነ ትመጠበቅ<br>5. የህጻናትደህንነ ትመጠበቂያዘ ዴዎች | - የክብርንምንነትአስመልክቶመነሻሀሳብበመስጠት ማወያየት<br>- በራስመተማመንናበራስመኩራትንበተመለከተየቀ ረቡምስሎችንበማቅረብምንእንደተረዱእንዲገልጹ ማድረግ<br>- ክብርንማሳያመንገዶችምንምንእንደሆኑከቀረቡት ምስሎችእንዲገነዘቡማድረግ<br>- ደህንነታችንንለአደጋከሚያጋልጡነገሮችእንዴት መጠንቀቅእንዳለብንምስሎችንበማቅረብማስገንዘብ<br>- ህጻናትደህንነታቸውንበተለያዩዘዴዎችመጠበቅእን ደሚችሉምስሎችንበማቅረብማስረዳት<br>- ለምዕራፉየተሰጡትንየክለሳጥያቄዎችበማቅረብት ምህርቱንተጨባጭማድረግ<br>- ምስሎችን፣ተንቀሳቃሽምስሎችንበመርጃመሳሪያነ | - የግንዛቤጥያቄበማቅረብሲ ወያዩምልከታማድረግ<br>- የተማሪዎችንብቃትምልከ ታበማድረግመመዝገብ<br>- የክፍልናየቤትስራመስጠ ት<br>- የተለያዩምስልሎችንመሰ ረትያደረጉየቃልጥያቄማ ቅረብ<br>- የክለሳጥያቄዎችንመስጠ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውንዜዴዎችትናገራለህ/ሽ::<br>✍ ሕፃናትደህንነታቸውንእንዴ ትእንደሚጠብቁትዘረዝራለህ/ ሽ፣ | | ትመጠቀም | ት<br>✍ የግልመመዘኛጥያቄዎች ንማቅረብ |

## ምዕራፍሁለት **እውነተኛነት እና ታማኝነት**

(ክፍለጊዜ 20)

### የሚጠበቁ የመማርውጤቶች

- የእውነተኛነትእናታማኝነት ምንነት መግለጽ፤
- የእውተኛነትእናየታማኝነትአመላካቾችንመናገር።

| ቢያንስሊጎናጸፉየሚገባቸውየመማርብቃቶች | የትምህርቱይዘት | የመማርማስተማርዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| - የእውተኛነትንእናየታማኝነትንምንነትትገልጻለህ/ሽ።<br>- የእውነተኛነትእናየታማኝነትማሳያዎችንትዘረዝራለህ/ሽ፤<br>- እውነትመናገርያለውንፋይዳትናገራለህ/ሽ።<br>- ቃልኪዳንማክበርያለውፋይዳትለያለህ/ሽ።<br>- መስረቅእናማጭበርበርየሚያስከትለውንጉዳትትለያለህ/ሽ። | 1. የእውነተኛነትእናየታማኝነትምንነት<br>2. የእውነተኛነትእናየታማኝነትማሳያዎች<br>3. ቃልኪዳንንማክበር<br>4. የመስረቅእናማጭበርበርንመጥላት | - ተማሪዎችእውነትመናገርምንጥቅምእንዳለውበቡድንተወያይተውእንዲገልጹማድረግ<br>- ተማሪዎችጥንድጥንድበመሆንየእውነተኛነትናየታማኝነትማሳያዎችላይእንዲወያዩ ፣ማድረግ.<br>- የቀረቡትንምስሎችከቀረቡትታሪኮችጋርእያዛመዱእንዲወያዩማድረግ<br>- በቡድንበመከፋፈልስለመስረቅናማታለልጉዳትእንዲወያዩማድረግ<br>- በተሰጡትመልመጃዎችላይእንዲወያዩማድረግ<br>- ምስሎችን፣ተንቀሳቃሽምስሎችንበመርጃመሳሪያነትመጠቀም | - ተማሪዎችቡድንሲወያዩምልከታማድረግ<br>- የተማሪዎችንብቃትመመዝገብ<br>- ክፍልናየቤትስራመስጠት<br>- የክለሳጥያቄመስጠት |

# ምዕራፍ ሶስት ፍትህ

(ክፍለጊዜ 20)

## የሚጠበቁየመማርውጤቶች

- የፍትህእናፍትሃዊነትምንነትንመግለጽ፣
- የፍትህእናፍትሃዊነትአስፈላጊነትመናገር፣
- ከፍትህጉድለትየሚመጣንጉዳትመለየትናቸው፡፡

.

| ቢያንስሊጎናጸፉየሚገባቸ ውየመማርብቃቶች | የትምህርቱ ይዘት | የመማርማስተማርዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| - የፍትህንምንነትት ለያለህ/ሽ፡፡<br><br>- የፍትሃዊነትን ምንነት ትለያለህ/ሽ፣ | 1. የፍትህ ምንነት<br><br>2. ፍትሃዊ ነት | - ተማሪዎችበፍትህምንነትላይእንዲወያዩማድረግ<br>- የቀረቡትንምስሎችበመመልከትየተረዱትንእንዲገልጹማድ ረግ<br>- የተለያዩታሪኮችንበማቅረብተማሪዎችእንዴትፍትሃዊነትን እንደሚጠብቁእንዲወያዩማድረግ<br>- የተለያዩምስሎችንናታሪኮችንበማቅረብተማሪዎችፍትሃዊነ ትንእንዴትእንደተረዱእንዲወያዩማድረግ<br>- መልመጃዎችንበመስጠትእንዲወያዩማድረግ<br>- የክለሳጥያቄዎችንእንዲሰሩማበረታታትግብረመልስመስጠ | - የክፍልስራመስጠት<br>- ምልከታበማድረግየተማሪዎ ችንለውጥመመዝገብ<br>- የቤትናየክፍልስራመስጠት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ት<br><br>✍ ምስሎችን፣ተንቀሳቃሽምስሎችንበመርጃመሳሪያነትመጠቀም | ✍ የክለሳጥያቄመስጠት |

# ምዕራፍአራት መልካም ማህበራዊ ግንኙነት

(ክፍለጊዜ 19)

## የሚጠበቁየመማርውጤቶች

- የመልካምግንኙነትን ምንነትትገልጻለህ/ጫለሽ፣
- መልካምግንኙነቶችንሊያጎለብቱ የሚችሉ ነገሮችን ትለያለህ/ሽ፣
- መልካም ጓደኝነትን የሚጎዱ ነገሮችን ትለያለህ/ሽ::

| ች | የትምህርቱይዘት | የመማርማስተማርዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| ትለያለህ/ሽ፣<br>ሮችአንዱእንደሆነትረዳለህ/ጃለሽ::<br>ለህ/ሽ | 1. ጓደኝነት<br>2. መረዳዳት<br>3. ጓደኝነትን የሚጎዱ ነገሮች | - የግንዛቤጥያቄዎችንበመጠየቅዳራዊእውቀታቸውንበመቀስቀስየጓደኝነትንምንነትናጓደኝነትንለማጠናከርምንምንእንደሚያደርጉበቡድንማወያየት<br>- ተማሪዎችምንምንበማድረግቤተሰባቸውንእንደሚረዱናመረዳዳትምንጥቅምእንዳለውበቡድንእንዲወያዩማድረግ<br>- ጓደኝነትንበሚጎዱነጥቦችላይእንዲወያዩማድረግ<br>- ለምዕራፉትምህርትማጠቃለያመስጠት<br>- የክለሳጥያቄዎችንመሰራት<br>- ምስሎችን፣ተንቀሳቃሽምስሎችንበመርጃመሳሪያነት መጠቀም | - የክፍልስራመስጠት<br>- የቤትስራመስጠት<br>- ምልከታበማድረግየተማሪዎችንለውጥመመዝገብ<br>- የክለሳጥያቄዎች |

# ምዕራፍ አምስት ለጋራ ንብረት መጠንቀቅ

(ክፍለጊዜ 20)

**የሚጠበቁየመማርውጤቶች**

- የጋራንብረትንመለየት
- የጋራንብረትንምንነትመግለጽ
- ለጋራንብረትቅድሚያመስጠት
- የጋራ ጥቅም እንቅፋቶች መለየት

| ቢያንስሊኅናጸፉየሚገባቸውየመ ማርብቃቶች | የትምህር ቱይዘት | የመማርማስተማርዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| የጋራንብረትየሆኑነገሮችንት ለያለህ/ሽ:: <br> ውሃየጋራሀብትመሆኑንትና ገራለህ/ሽ:: <br> የውሃንንጽህናመጠበቅየማን ድርሻእንደሆነትገልጻለህ/ሽ:: <br> ትምህርትቤትየጋራንብረት መሆኑንትገልጻለህ/ሽ:: <br> መንገድየጋራንብረትመሆኑ ንትገልጻለህ/ሽ:: | 1. የጋራ ንብረ ት <br> 2. ውሃ <br> 3. ትም ህርት ቤት <br> 4. መንገ ድ | የግንዛቤጥያቄዎችንማሰራትዳራዊእውቀታቸውንበመቀስቀስየጋ ራንብረትማለትምንማለትእንደሆነእንዲወያዩማድረግ <br> ተማሪዎችየውሃንጽህናመጠበቅበተመለከተእንዲወያዩማድ ረግናተገቢግብረመልስመስጠት <br> ከጋራንብረቶችትምርትቤትአንዱመሆኑንናሌሎችየጋራንብ ረትየሆኑትንእንዲዘረዝሩማድረግ <br> የትምህርትቤትናየመንገድንምስልከመማሪያመጽሀፉላይበ መመልከትየተገነዘቡትንተወያይተውእንዲናገሩማድረግ <br> መልመጃዎችንናየክለሳጥያቄዎችንማቅረብናማወያየት | የቃልጥያቄመጠየቅ <br> ምልከታበማድረግየተማ ሪዎችንለውጥመመዝገብ <br> የክፍልናየቤትስራመስ ጠት <br> የክለሳጥያቄዎችንማቅረ ብናግብረመልስመስጠት |

# ምዕራፍ ስድስት ባህላዊ ቅርሶች

(ክፍለጊዜ 20)

**የሚጠበቁየመማርውጤቶች**

- ባህላዊ ቅርሶች ምን እንደሆኑ መናገር፤
- የተለያዩ ባህላዊ ቅርሶችን መለየት፤
- ባህላዊ ቅርሶችን መንከባከብ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት፤
- ለባህላዊ ቅርሶቸ የሚደረጉትን እንክብካቤዎች መለየት ናቸው።

| ቢያንስሊጎናጸፉየሚገባቸውየመማርብቃቶች | የትምህርቱይዘት | የመማርማስተማርዘዴ | ምዘና |
|---|---|---|---|
| - ባህላዊ ቅርሶችን ትለያለህ/ሽ።<br>- ባህላዊቅርስአይነቶችንትዘረዝራለህ/ሽ።<br>- የባህላዊቅርሶችንጥቅምትናገራለህ/ሽ።<br>- ባህላዊቅርሶችንእንዴትመንከባከብእንደሚኖርባችሁትናገራለህ/ሽ። | 1. የባህላዊ ቅርሶች ምንነት<br>2. የባህላዊቅርስዓይነቶች<br>3. የባህላዊቅርስጥቅም<br>4. የባህላዊ ቅርስ ጥቅም | - ለግንዛቤየቀረበውንጥያቄበማቅረብበባህላዊቅርሶች ምንነትላይእንዲወያዩማድረግ<br>- የተለያዩየባህላዊቅርስአይነቶችንምስሎችበማቅረብ ከምስሉየተገነዘቡትንእንዲናገሩማድረግ<br>- ተማሪዎችበባህላዊቅርስጥቅሞችላይእንዲወያዩማ ድረግ<br>- ተማሪዎችበክለሳጥያቄዎችላይእንዲወያዩማድረግ | - የቃልጥያቄ<br>- ምልከታማድረግናየተማሪዎ ችንለውጥመመዝገብ<br>- የክፍልናየቤትስራመስጠት<br>- የክለሳጥያቄዎችንማቅረብ |